# በእርሱ ፈቃድ በአባቱ ፈቃድ

## በእርሱ ፈቃድ በአባቱ ፈቃድ በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ
## ከሰማያት ወረደ ከድንግል ማርያም ተወለደ

ዓለሙን እንዲሁ ወደደና
ከሰማያት በላይ ወረደና
በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት
ተወሰነ አምላከ አማልክት
ከሰማያት የወረደው ፍቅር ስቦት የመጣው
ወልደ አብ ወልድ ማርያም ኢየሱስ ፈራጅ ነው

በእርሱ ፈቃድ በአባቱ ፈቃድ በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ
ከሰማያት ወረደ ከድንግል ማርያም ተወለደ

ቅድመ ዓለም ተወልዶ ያለ እናት
ድህረ ዓለምም ያለ አባት
የእግዚአብሔር ልጅ በእርግጥም ሰው ሆነ
ሁሉ በእርሱ ይኸው ተከናወነ ተከናወነ
ከሰማያት የወረደው ፍቅር ስቦት የመጣው
ወልደ አብ ወልድ ማርያም ክርስቶስ አምላክ ነው

## በእርሱ ፈቃድ በአባቱ ፈቃድ በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ
## ከሰማያት ወረደ ከድንግል ማርያም ተወለደ

የማይታይ ታየ በምድር
እረቂቁ ገዘፈ ስለፍቅር
ሥጋን ተዋህዶ ሆነልን ፈውስ
አማኑኤል የነገሥታት ንጉሥ
ከሰማያት የወረደው ፍቅር ስቦት የመጣው
ወልደ አብ ወልድ ማርያም እግዚአብሔር እሱ ነው

✞✞✞ ✞✞✞ ✞✞✞

# እግዚአብሔር መልካም ነው

እግዚአብሔር መልካም ነው
በመከራ ቀንም መሸሸጊያ ነው(፪)

ከገነት ሲሰደድ አዳም አባታችን
ሞት ነግሶብን ሳለ በእኛ በሁላችን
ቃል እንደገባለት ተወልዶ ሊያድነው
በመከራ ጊዜ መሸሸጊያ ሆነው(፪)

**እግዚአብሔር መልካም ነው**

**በመከራ ቀንም መሸሸጊያ ነው(፪)**

አብርሃም ከካራን ከእናት ከአባቱ ቤት

ከነአን ሲገባ ሲሰደድ በእምነት

ከተሰጠው ተስፋ አንዳች ሳይጎልበት

እንደ ምድር አሸዋ ዘሩን አበዛለት(፪)

## እግዚአብሔር መልካም ነው
## በመከራ ቀንም መሸሸጊያ ነው(፪)

በሐዘን በችግር በመከራ ጊዜ
ጭንቀቴን የሚያርቅ ነው የፍሴን ትካዜ

የቀደመው እባብ ሰላሜን ሲነሳኝ

እግዚአብሔር መልካም ነው ሐዘኔን አስረሳኝ

የቀደመው እባብ ሰላሜን ቢነሳኝ

ክርስቶስ ኢየሱስ ሐዘኔን አስረሳኝ

መዘንጋት ባለበት በታናሽ ሕሊና
መዘመር ልጀምር ለድንግል ምስጋና
እኔስ በውዳሴሽ ባሕር እዋኛለሁ
ገናንነትሽን ክብርሽን እያሰብኩ

የትህትናሽ ነገር ቢወሳ አያልቅም
ታነቢያለሽና ለዚህ ክፉ ዓለም
ድንግል ሆይ ለኃጥአን ታስቢያለሽና
ልቦናዬ በአንቺ በምልጃሽ ተጽናና

መዘንጋት ባለበት በታናሽ ሕሊና
መዘመር ልጀምር ለድንግል ምስጋና
እኔስ በውዳሴሽ ባሕር እዋኛለሁ
ገናንነትሽን ክብርሽን እያሰብኩ

ማርያም ሆይ ስለዚህ እንወድሻለን
አንቺን ተማጽነናል እንድታማልጂን
ዘወትር እጆችሽ ተዘርግተዋልና
ስለበደለኞች ሊያቀርቡ ልመና

መዘንጋት ባለበት በታናሽ ሕሊና
መዘመር ልጀምር ለድንግል ምስጋና
እኔስ በውዳሴሽ ባሕር እዋኛለሁ
ገናንነትሽን ክብርሽን እያሰብኩ

እሳታውያኑ ሱራፌል ኪሩቤል
ሊነኩት ያልቻሉት የእሳቱን ነበልባል
አንቺ ግን ታወፍሽው ሳምሽው በከንፈርሽ
ከፍጥረት ለይቶ ፍፁም ስለአፀናሽ

መዘንጋት ባለበት በታናሽ ሕሊና
መዘመር ልጀምር ለድንግል ምስጋና
እኔስ በውዳሴሽ ባሕር እዋኛለሁ
ገናንነትሽን ክብርሽን እያሰብኩ

ማርያም ሆይ ስለዚህ እንወድሻለን
አንቺን ተማጽነናል እንድታማልጂን
ዘወትር እጆችሽ ተዘርግተዋልና
ስለበደለኞች ሊያቀርቡ ልመና

✞✞✞ ✞✞✞ ✞✞✞